Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፭
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.75
ADDIS ABABA August 18th, 2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፬/፪ሺ፲፪

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን (ለማሻሻል)..........................................................ገፅ ፲፪ሺ፯፻፳፮

**Content**

Proclamation No. 1224/2020

Ethiopian Human Rights Commission Establishment (Amendment) Proclamation Page .....…………………12726

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፬/፪ሺ፲፪

## የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የተቋቋመበትን የሰብዓዊ መብቶችን ግንዛቤ የማስፋፋት፣ የማስጠበቅ እና የማስከበር ሥራ በተገቢው መንገድ እንዲያከናውን ማስቻል እና የማስፈጸም አቅሙን ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ለዚህም ይረዳ ዘንድ የኮሚሽነሮች አመራረጥ እና አሿሿም አሳታፊና ግልጽ ማድረግና የኮሚሽኑን የመዋቅር፣ የሠራተኛ ቅጥርና አስተዳደር እንዲሁም የበጀት ነፃነት ማረጋገጥን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ማሻሻልና የተቋሙን ተዓማኒነት፣ ተቀባይነት እና ውጤታማነት ማጐልበት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና ፶፭(፲፬) መሠረት የሚከተለው ማሻሻያ ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO 1224/2020

## ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION ESTABLISHMENT PROCLAMATION (AMENDMENT)

**WHEREAS,** it is necessary to strengthen the Ethiopian Human Rights Commission's institutional and execution capacity to enable the Commission to fulfill its mandates of promoting, ensuring the respect of and protection of Human Rights in Ethiopia;

**WHEREAS**, it is also found necessary to make nomination and appointment process of Commissioners participatory and transparent in addition to making improvements to provisions related to the structure of the Commission, hiring and management of staff and the budgetary independence of the Commission in order to enhance public trust, acceptance and effectiveness of the Commission ;

**NOW, THEREFORE**; in accordance with Article 55(1) and 55(14) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፬/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፲/፲፱፻፺፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪(፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፪(፩) ተተክቷል፡፡

"(፩) ተሿሚ ማለት በአዋጁ መሠረት በምክር ቤቱ የሚሾም የሰብዓዊ መብቶች ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና የሴቶችን እና ህፃናትን ጉዳይ የሚከታተል ምክትል ኮሚሽነር እንዲሁም ሌሎች የልዩ ልዩ ሰብዓዊ መብቶች ዘርፍ ኮሚሽነሮች ማለት ሲሆን የዘርፍ ኮሚሽነሮች፣ የአካል ጉዳተኞች፣የሲቪልና ፖለቲካ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚ መብቶች ጉዳይን ይጨምራል፡፡"

፪. የአዋጁ አንቀጽ ፮ ስር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፮(፲፩) — ፮(፲፫) ተጨምረው፤ የቀድሞው ንዑስ አንቀጽ ፮(፲፩) ንዑስ አንቀጽ ፮(፲፬) ሆኖ ተስተካክሏል፤

"፮(፲፩) በምርጫ ወቅት የሰብዓዊ መብቶች አጠባበቅን ክትትል ማድረግ፤

፮(፲፪) በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መርማሪ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ስለሰብዓዊ መብቶች አጠባበቅ ሁኔታ ክትትል ማድረግ፤

፮(፲፫)በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውንም ማረሚያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች ወይም በቁጥጥር ወይም በእገታ ስር የሚገኙ ሰዎች ያሉበትን ስፍራ እንዲሁም እንደ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣መጠለያ ጣቢያ፣ የገበያ ማዕከል የመሳሰሉ እና የሕዝባዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ያለ ቅድመ ማስታወቂያ መጎብኘት፡፡"

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Human Rights Commission Establishment (Amendment) Proclamation No.1224/2020.

**2. <u>Amendment</u>**

The Ethiopian Human Rights Commission Establishment Proclamation No. 210/2000 is hereby amended as follows:

1/ Article 2(1) is repealed and replaced as follows:

" (1) Appointee means the Chief Commissioner for Human Rights, the Deputy Chief Commissioner, Deputy Commissioners for Women and Children Affairs and other Commissioner heading different thematic Human Rights areas appointed by the House in accordance with the Proclamation. Thematic areas include disability rights, civil and political rights and socio economic and cultural rights."

2. The following new Sub Articles 6(11) – 6(13) are added under Article 6 of the Proclamation and the former Article 6(11) is accordingly amended as Article 6(14);

"6(11) Monitor the Human Rights situation during election periods;

6(12) Without prejudice to the power vested on the State of Emergency Inquiry Board, monitor the Human Rights situation during state of emergency;

6(13) Visit and monitor, without prior notice, any correction centers or prisons, police detention centers or any place where people are held in custody or otherwise detained anywhere in the country as well as any public service institution such as schools, hospitals, shelter camps and market centers."

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief


፫. የአዋጁ አንቀጽ ፰(፪)(መ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፰(፪) (መ) ተተክቷል፡፡

"፰(፪) (መ)ሌሎች ከአራት ያላነሱ የልዩ ልዩ ሰብዓዊ መብቶች ዘርፍ ጉዳዮችን የሚመሩ ኮሚሽነሮች"

፬.የአዋጁ አንቀጽ ፱ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፱ ተተክቷል፡፡

"የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ በኮሚሽነሮች ጉባዔ ውሳኔ አሁን ካሉት ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶች በተጨማሪ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወይም እንደሁኔታው መለስተኛ የኮሚሽኑ ማዕከሎች ሊኖሩት ይችላል፡፡"

፭. የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፩ ተተክቷል፡፡

"፲፩(፩) የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ…………………………….....ሰብሳቢ፣

ለ)የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት……………..ም/ሰብሳቢ፣

ሐ)በምክር ቤቱ መቀመጫ ካላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በጋራ ስምምነት የሚመረጥ አንድ ሰው………አባል፣

መ)ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አባላት አንድ ሰው………አባል፣

ሠ) ከኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋሟት ጉባዔ አንድ ሰው……አባል ፣

ረ) ከፌደሬሽን ምክር ቤት አንድ ሰው…..………………….አባል፣

ሰ).ከሲቪል ማህበራት አንድ ሰው………………………….አባል፣

፲፩(፪) የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ አባላት ገለልተኛነታቸውና ብቃታቸው የተረጋገጠ፣ እንደ አግባብነቱ በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ስር የተዘረዘሩትን ለኮሚሽነርነት የሚያበቁ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

፲፩(፫) ኮሚቴው የራሱን መንገድ በመጠቀም እንዲሁም ግልጽና አሳታፊ አሰራር በመዘርጋት በሕዝብ ጥቆማ ከቀረቡ ሰዎች ውስጥ፣ መስፈርቱን የሚያሟሉ በአብላጫ ድምፅ የተደገፉ ዕጩዎችን ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡ የዕጩዎች ዝርዝር በተቻለ መጠን የልዩ ልዩ ሕብረተሰብ ክፍሎች እና የጾታ ስብጥርን ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡"

3. Article 8(2) (d) is repealed and replaced as follows:

"8(2) (d) Not less than four Commissioners heading human rights thematic areas"

4. Article 9 is repealed and replaced as follows:

"The Commission shall have its Head Office in Addis Ababa and it may have additional branch offices or centers at any place as determined by the Council of Commissioners".

5. Article 11 is repealed and replaced as follows:

"11(1).The Nomination Committee shall have the following members:

a. The Speaker of the House …………….Chairperson;

b. The President of the Federal Supreme Court….Deputy Chairperson;

c. One member of the House to be elected by the joint agreement of opposition parties having seats in the House………………………………………Member;

d. One member of the National Electoral Board of Ethiopia……………………………………...Member;

e. One member from the Ethiopian Inter-Religious Council; ……………………………………Member;

f. One member from House of Federation , and

g. One member from Civil Society Organizations.

11(2) Nominating Committee shall have independent and competent members who shall also fulfill the criteria, as appropriate, for appointment of Commissioner under Article 12 of the Proclamation.

11(3) The Nominating Committee shall follow a transparent and participatory public nomination process as well as use its own means to identify suitable candidates and submit to parliament nominees it has selected by a majority vote. To the extent possible, the list of nominees should take into consideration gender diversity and representation from different parts of the society."

፮. የአዋጁ አንቀጽ ፲፪(፯) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፪(፯) ተተክቷል፡፡

"፲፪(፯) የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ"፡፡

፯. አንቀጽ ፲፰ ስለ ኮሚሽነሮች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች እና ተጨማሪ የሙያ ሥራ መስራት የተከለከለ ስለመሆኑ

"፲፰(፩) የዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና ሌሎች ኮሚሽነሮች ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅሞችን በተመለከተ በመንግስት የከፍተኛ የመንግስት ተሿሚዎች ደሞዝና ጥቅማጥቅም መሰረት ይፈፀማል፡፡

፲፰(፪) ተሿሚው በስራ ዘመኑ በማናቸውም ክፍያን በሚያስገኝ በሌላ የመንግስትም ሆነ የግል ቅጥር ስራ ላይ መሰማራት አይፈቀድለትም፡፡"

፰. የአዋጁ አንቀጽ ፲፱(፪) ስር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (ተ) ፣ (ቸ) ፣ (ነ) እና (ኘ) ተጨምረዋል፡፡

"(ተ) የኮሚሽኑን የውስጥ አደረጃጀት እና መዋቅር፣ በዘርፍ ኮሚሽነሮች መካከል ያለውን የሥራ ክፍፍልና የዘርፍ ኮሚሽነሮችን የሥራ መደብ ይወስናል፤

ቸ) የኮሚሽነሮች ጉባዔን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፡፡

ነ) ዳይሬክተሮችንና ሌሎች የሥራ ክፍል ኃላፊዎችን ይመድባል፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውን የኮሚሽነሮች ጉባዔ በሚያወጣው ዝርዝር የሥራ መመሪያ መሠረት ይወስናል፤

ኘ) የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኃላፊዎችን እንዲሁም ከኮሚሽነሮች ጉባዔ ጋር በመመካከር ለኮሚሽኑ ተጠሪ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ልዩ ዘጋቢዎች ይመድባል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በኮሚሽነሮች ጉባዔ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡"

6. Article 12(7) of the Proclamation is repealed and replaced as follows:

"12(7) Is not a member of a political organization."

7. Article 18 Salary and other Benefits of Commissioners and Other Professional Work shall be prohibited

"18(1) The Chief Commissioner, Deputy Chief Commissioner and other Commissioners shall be entitled to the benefits and privileges determined in accordance with the law provide for the benefits of Government Higher officials.

18(2) An appointee shall not be allowed to engage in other gainful, public or private employment during his term of office. "

8. Article 19(2) is amended to include the following new Sub Articles (k), (l), (m) and (n):

" k) Determine the internal organizational structure of the Commission, assign the specific post of thematic Commissioner's and decide on the division of roles and responsibilities among them;

l) Call and preside over the meetings of the Council of Commissioners;

m) Appoint department Directors and other Senior Officers and determine their roles and responsibilities in accordance with the work Directives adopted by the Council of Commissioners;

n) Appoint heads of branch offices and Human Rights Special Rapporteurs accountable to the Commission in consultation with the Council of Commissioners. The particulars shall be determined by Directives to be issued by the Council of Commissioners. "

Abrham Yohanes
https://t.me/ethiopianlegalbrief



፱. የአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ርዕስ እና አንቀጽ ፳፩ ተተክቷል፡

"፳፩. የልዩ ልዩ ሰብዓዊ መብቶች ዘርፍ ኮሚሽነሮች ሥልጣን እና ተግባር

የዘርፍ ጉዳይ ኮሚሽነሮች በዋናው ኮሚሽነር አማካኝነት የሚመደቡበትን የስራ ዘርፍ በኃላፊነት ከመምራት በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ሀ) ከዋናው ኮሚሽነር ጋር በመመካከር የሥራ ዘርፉን ማደራጀትና ማስተዳደር፤

ለ) የሥራ ዘርፉን ሠራተኞች መከታተልና መምራት፤

ሐ) የሚመሩትን ዘርፍ ወቅታዊና ዓመታዊ ክንዋኔ ሪፖርት ለዋና ኮሚሽነሩ ማቅረብ ፤

መ) በዋና ኮሚሽነሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡፡"

፲. የአዋጁ አንቀጽ ፳፭ ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፳፭(፬) ተጨምሯል፡፡

"፳፭(፬) ማንኛውም ለኮሚሽኑ ጥቆማ ያቀረበ ወይም ምስክር ሆኖ የሚቀርብ ሰው እንደአግባብነቱ ስለወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች ጥበቃ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፱/፪ሺ፫ የተመለከተው አይነት ጥበቃ ወይም በፍርድ ቤት ለሚቀርብ ምስክር ያለው ዓይነት መብት እና ጥበቃ ይደረግለታል፡፡"

፲፩. አዋጁ አንቀጽ ፴፩(፫) እስከ (፯) ያሉት ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፴፩(፫) እስከ ፴፩(፰) ተተክተዋል፡፡

"፴፩(፫) የኮሚሽኑን የሰው ሀብት፣ የንብረትና የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያዎች እንዲሁም የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ የሠራተኞች አስተዳደር መመሪያን ያፀድቃል፤

፴፩(፬) የኮሚሽኑን የሰብዓዊ መብቶች ሥራ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ያፀድቃል፤



9. Article 21 is repealed and replaced as follows with a new title:

"21. Powers and Duties of Thematic Commissioners

In addition to heading the thematic area of human rights work they have been assigned to by the Chief Commissioner, the thematic Commissioner have the following duties and responsibilities:

a. Organize, oversee, and administer the activities in their respective thematic areas in consultation with the Chief Commissioner;

b. To lead and manage staff assigned to the thematic area;

c. Submit periodic and yearly activity and performance reports to the Chief Commissioner on their respective thematic areas;

d. Carry out other activities as may be assigned by the Chief Commissioner. "

10. Article 25 is amended including a new sub Article 25(4) as follows:

"25(4) Any witness appearing before the Commission or a whistleblower is afforded the same rights and protection as provided under the 'Protection of Witnesses and Whistleblowers of Criminal Offences Proclamation No. 699/2010' or as witnesses appearing before a court of law, as appropriate."

11. Articles 31(3) to (7) are repealed and replaced with new Sub Articles 31(3) to (8) as follows:

"31(3) To issue Directives and adopt Rules of Procedures and manuals on management of human resources, property and finance, as well as on administration of staff of the Commission based on Federal Civil Service principles ;

31(4) To adopt policies and strategies relating to its activities and the human rights mandates of the Commission;

Abrham Yohanes https://t.me/ethiopianlegalbrief

፴፩(፭) የሠራተኞች የአስተዳደር ቅሬታዎች የሚጣራበትና የሚወሰንበት ሥርዓትና መመሪያ ያፀድቃል፣ በሠራተኞች የአስተዳደር ቅሬታዎች ላይ በይግባኝ ሰሚ ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፴፩(፮) በዋና ኮሚሽነሩ አቅራቢነት የኮሚሽኑን የውስጥ ኦዲተር ይመድባል፣

፴፩(፯) የሠራተኞችን የሥነ ምግባር መመሪያ እና ጥቅማ ጥቅም ያፀድቃል፣

፴፩(፰) የጉባዔው ውሳኔዎች በአባላት ድምፅ ብልጫ ይወሰናሉ፣ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የሚከፈል ከሆነ ዋና ኮሚሽነሩ የደገፈው ሀሳብ የጉባዔው ውሳኔ ይሆናል፡፡”

፲፪. የአዋጁ አንቀጽ ፴፪ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፪ ተተክቷል፡፡

“፴፪. በሠራተኞች አስተዳደር ጉዳይ ላይ የኮሚሽነሮች ጉባዔ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በ፴ ቀናት ውስጥ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሊታይ ይችላል፡፡”

፲፫. የአዋጁ አንቀጽ ፴፮(፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፮(፪) ተተክቷል፡፡ እንዲሁም የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፴፮(፫) ተጨምሯል:-

“ ፴፮(፪) ገንዘብ ሚኒስቴር ምክር ቤቱ ለኮሚሽኑ ያፀደቀለትን ዓመታዊ በጀት ኮሚሽኑ የፋይናንስ አሰራርን ተከትሎ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት በየሶስት ወሩ የሚያስፈልጋቸውን በጀት በቅድሚያ ወደ ኮሚሽኑ የባንክ ሂሳብ ማስገባት አለበት፡፡

፴፮(፫) የመንግስት የፋይናንስ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ በኮሚሽነሮች ጉባኤ በሚፀድቅ የውስጥ ደንብ ኮሚሽኑ በጀቱን የማስተዳደር ሙሉ ነፃነት አለው፡፡”

31(5) To adopt rules of procedures and Directives for consideration and determination of staff administrative complaints including appeal procedures and the Council of Commissioners serving as the final appellate tribunal for administrative complaints;

31(6) To appoint an internal Auditor upon the recommendation of the Chief Commissioner;

31(7) To adopt code of ethics for staff and approve their benefit packages;

31(8) The decision of the Council shall be made by majority vote. On instances of a tie, however, the Chief Commissioner shall have a casting vote. ”

12. Article 32 is repealed and replaced as follows:

“32 A staff member dissatisfied by the final decision of the Council of Commissioners on administrative complaints may appeal to the Federal High Court within 30 days from receipt of the decision.”

13 Article 36(2) is repealed and replaced as follows and the following sub-Article 36(3) is added:

“36(2) As per the annual budget of the Commission approved by the House and based on request from the Commission in accordance with the finance Regulations, the Ministry of Finance shall deposit the 3 month quarterly budget in advance to the bank account of the Commission.

36(3) In accordance with internal financial rules and Directives to be adopted by the Council of Commissioners, the Commission has full financial autonomy to administer its budget.”

**፫. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ቀን አንስቶ የጸና ይሆናል፡፡

**3. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the day of its approval by the House of People's Representatives.

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

**Done at Addis Ababa On this 18th day of August, 2020.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**